## ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 35 ኛ ሳምንት
# ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን አጠመቀው

**ዓላማ**
- ❖ ስለኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ጥምቀት ታሪክና ወደ ኢየሩሳሌም ስላደረገው ጉዞ መማር።

**የሚጠና ጥቅስ**
- ❖ *"እንደበግ ወደ መታረድ ተነዳ፣"* የሐዋ.ሥ 8 ፥ 32

**ምንባብ**
- ❖ የሐዋ.ሥ 8፥26-40

**መግቢያ**
- ❖ ከአይሁድ ምድር ቀጥሎ ክርስትናን የተቀበለች የመጀመሪያዋ ሀገር ናት ኢትዮጵያ።
- ❖ ዛሬም የንግስቲቱ ባለ ሙሉሥልጣን የነበረው የመጀመሪያው ክርስቲያን እንዴት እንዳመነና እንደተጠመቀ እንማራለን።

**ትምህርቱ**
- ❖ ኢትዮጵያውያን ከክርስትና በፊትም አምልኮታቸውን ለመፈጸም ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር።
- ❖ ክርስቶስ በዐረገ በአመቱም የንግስት ህንደኬ/ የዚያን ጊዜዋ የኢትዮጵያ ንግስት/ በሐብትዋ ሁሉ ላይ ባለሙሉ ስልጣን የነበረው ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ሲመለስ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።
- ❖ ያነብ የነበረው የመጽሐፍ ክፍልም ጌታ ከመሠቀሉ ከመቶ አመታት በፊት በነቢያት የተነገረ የመስቀል ትንቢት ነበር። የጌታም መልአክ ፊልጶስ ጃንደረባው በሚሄድበት መንገድ ሄዶ እንዲሰብክለት ነገረው።
- ❖ መንፈስ ቅዱስም ፊልጶስን ነጥቆ ወሰደው። ጃንደረባው ጋር ሲደርስም ነቢዩ ኢሳይያስ ስለክርስቶስ መከራ መሰቀል *"እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፣ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም።"* ሲል የተነበየውን ያነብ ነበር።
- ❖ ፊልጶስም ቀርቦ *" የምታነበውን ታስተውለዋለህ"* ሲለው *"የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው።"* ወደ ሰረገላውም ገብቶ እንዲያስተምረውም ጠየቀው ፊልጶስም ከነቢዩ የትንቢት ቃል ጀምሮ ስለ ክርስቶስ ከእመቤታችን መወለድ፣ማስተማር፣ መሰቀል ትንሳኤና ዕርገቱንም አስተማረው።
- ❖ በመንገድ ሲሄዱም ውሃ ካለበት ቦታ ደረሱ በዚህ ግዜ ጃንደረባው *"እነሆ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድርነው?* አለው። ፊልጶስም መልሶ *" በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል"* አለው።*" ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ"* አለ ጃንደረባው።
- ❖ ሁለቱም ከሰረገላው ወረዱ፣ፊልጶስም ኢትዮጵያዊውን አጠመቀው፣የመጀመሪያው እስራኤላዊ ያልሆነ ተጠማቂም ሆነ። ከውሃው ሲወጡም ፊልጶስ ወዲያው በመንፈስ ቅዱስ ተነጥቆ ተወሰደ፤ ኢትዮጵያዊውም ደስ እያለው ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

**ከዚህ ታሪክ ምን እንማራለን?**
- መፅሐፍ ቅዱስ በምሥጢር የተሞላ ነው። የሚያስረዳን ሳይኖር ሊገባን አይችልም። ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊው *"የሚረዳኝ ሳይኖር እንዴት ይቻለኛል"* ያለው። እንዲያስረዳው ስለጠየቀም ፊልጶስ ስለክርስቶስ ነገረው። መጽሐፉን ተርጎመለት አምኖም ተጠመቀ።
- ነቢዩ ኢሳይያስ የተነበየውና ኢትዮጵያዊው ያነበው የነበረው የመጽሐፍ ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በትኅትና ባዶ አድርጎ በሚሰድቡት እንዳልዛተ ይነግረናል። ጸለየላቸውም እንጂ።
- እኛም ለሌሎቹ እንዲሁ ማድረግ አለብን ልንጸልይላቸው የሚገባን መልካም ለሚያደርጉልን ብቻ ሳይሆን ክፉ ለሚያደርጉብንም ነው።
- ጸሎታችን መልካም እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። ባይመለሱም እግዚአብሔር ለፍቅራችን እና ለመልካምነታችን ይከፍለናል።

**ጥያቄዎች**፡-

1. ጌታ በዐረገ በአመቱ የተጠመቀው ኢትዮጵያዊው ማነው? ማንስ አጠመቀው?
2. ኢትዮጵያዊው ያነብ የነበረው ምንድነው?
3. በፊልጶስና በኢትዮጵያዊው መሐል የተደረገውን ንግግር ለመምህር አስረዱ?
4. ፊልጶስ አገልግሎቱን ከፈጸመ በኋላ የት ሄደ?
5. መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ትርጓሜ ለምን ያስፈልገናል?

7. ሰማዕትነት ምንድነው?

**ይቆየን፡፡**